EthioLion

**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ. ም.

# በሕዝብ ጠላት ላይ እንረባረብ

ኢሕአፓ በተደጋጋሚ ባሰማቸው ጥሪዎች ከወያኔ አገዛዝ ጎን የተሰለፉ ወደ ሕዝብ ጎራ እንዲቀላቀሉ፤ ለወያኔ አገዛዝ ታዛዥ የሆነው ሠራዊት ጠመንጃውን በወያኔ ላይ እንዲወድር የብአዴን ቡድን አባላት የወያኔ አገዛዝ መጫወቻ መሆናቸውን በቃ እምቢ ብለው ከሕዝብ ጎን እንዲቆሙ፤ ወጣቶች ታሪካዊ ግዴታቸውን እንዲወጡና ለሕዝብ እንዲታገሉ፤ የትግራይ ተወላጆች ከወያኔ ቡድን ራሳቸውን እንዲያገሉ--እንዲርቁ፤ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ኃይሎች መለስተኛ ልዩነቶችን በአግባቡ በሁለተኛ ደረጃ ይዘው በዋና ጠላት ላይ እንዲረባረቡ አሳስቧል፡፡ ዛሬም መሰል ጥሪዎችን ደግሞ ከማሰማት ውጪ አማራጭ የለውም፡፡ በወያኔ አገዛዝ ላይ ሰፊው ሕዝብ በተባበረ መልክ መነሳት አለበት፡፡

የወያኔ አገዛዝ ቀውስ እየተባባሰ በመምጣቱ ቁንጮ መሪዎቹ ሕዝብን ለማደናገር በዚህም በዚያም እየጮሁ መሆናቸው ይታያል፡፡ አሰብን እናስመልሳለን፤ ለግንጠላ አልቆምንም፤...ወዘተ በሚል የሀሰት አቋምን በማስተጋባትና ለሀገር የታገሉትን ድርጅቶች በማውገዝ በማብጠልጠል፤ ለዚሁም እርኩሰ ግባቸው የለመደባቸውን ቅጥረኞች በማሰለፍ ዘመቻቸውን አጧጡፈዋል፡፡ ይህን ዘመቻ ውድቅ ማድረግ ሀገራዊ ግዴታችን ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የወያኔ ጎራ ጠላት ማነው የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እንዳያገኝ በተጠናከረ ደረጃ እየጣረ ነው፡፡ የሀገርና የሕዝብ ዋና ጠላት የወያኔ አገዛዝ ነው፡፡ በዚህ ላይ ምንም ብዥታ ሊኖረን አይገባም፡፡ ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ በአንድ በኩል ለሀገርና ለሕዝብ ታጋይ ነን እያሉ በሌላ በኩል ግን ወደ ወያኔ ለስለስ በሕዝብ ወገኖች ላይ ከረር ማለትን የሚሰብኩ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በአካባቢያችን ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ህልውና ተፈታታኝ የሆኑ ኃይሎችና አገዛዞች የነበሩና ያሉ ቢሆኑም ከእነዚህ በፊት ዋና ጠላታችን የሀገራችን የራሳችን ጠማማ ማለትም በሥልጣን ያለው አገዛዝ ብቻ ነው፡፡ ወያኔ ግን ዕይታችን ወደ ሌላ እንዲሆን እየጣረ ነውና

EthioLion.com

አሥመራ፥ ሞቃዲሾ አልቃይዳ ወይ ሌላ ቢለን ወግድ ብለነው የሕዝብና የሀገር ጠላት አንተው ወያኔ ነህ ማለት መቻል አለብን። ለዚህም ነው የወያኔን አገዛዝ በሰበብ አስባቡ መተንፈሻ ቀዳዳ ሊሰጡ የሚራወጡትንም ራሳቸውንም ተቃዋሚ አሉ አላሉ አጋልጠን ከሕዝብ ጎራ እንዳይደባለቁ ማገድ ያለብን። ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ማን መሆናቸው በጥንቃቄ ተለይቶ የሕዝብም ሙሉ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል። ትላንት የሕዝብ ነን ብለው ዶሮ ሶስቴ ሳይጮህ መቀመጫችን ከወያኔ ፓርላማ ነው ያሉትን ልንዘነጋ አይገባንም።

የወያኔ አገዛዝ ጠላት ከወደ ሞቃዲሾ ሊመጣ ነውና ደግፉኝ እያለ ስንቱን ዜጋ በማያገባው ጦርነት ማግዶ አስጨርሷል፤ እያስጨረሰም ነው። የድንበር ጦርነት ብሎ ከመቶ ሺ ያላነሰ ዜጋን ካስፈጀ በኋላ ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅና ጠላት እኔ አይደለሁም ብሎ ሲቀልድ የቆየነውን አሳፋሪ ታሪኩንና ማን አዲስ አበባ ድረስ አጅቦ እንዳደረሰውም እንድንረሳ ይፈልጋል። ከትግል አንፃር ግን የሕዝብና የሀገር ጠላት ማን እንደሆነ ወሳኝ በሥልጣን ያለውና ሕዝብን እየበደለ ያለው አገዛዝ ሳይሆን ጭቁኑ ሕዝብ ራሱ ብቻ ነው። ይህን የሕዝብ መብት ማስነጠቅ አይገባም። በመሆኑም ሁሉም ሀገር ወዳድ ኃይሎች በሀገርና ሕዝብ ዋና ጠላት ማለትም በወያኔ አገዛዝ ላይ እንዲረባረቡ ኢሕአፓ እንደገና ጥሪውን ያስተላልፋል።

EthioLion.com

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France